

# ኪንዲ (መዋለ ህጻናት) በኩውንስላንድ

## ኪንዲ ምንድን ነው?

ኪንዲ በመባልም የሚታወቀው ኪንደርጋርደን፣ ከየመዋለ ህጻናት ትምህርት በፊት ባለው ዓመት (በክዊንስላንድ የመጀመሪያ ዓመት ትምህርት) ለልጆች በፈረቃ ጊዜ የሚሰጥ የትምህርት መርሐ ግብር ነው። ኪንዲ ልጃችሁ የልጅነት ትምህርታቸውን ፣ ደህንነታቸውንና እድገታቸውን በሚደግፉ የጨዋታ ተሞክሮዎችና ግንኙነቶች አማካኝነት የሚማሩበት ቦታ ነው።

ህጻናት በኪንዲ በመሳተፍ የመማር ፍቅር ያዳብራሉ እናም ወደ ቅድመ ትምህርት በሚሸጋገሩበት ጊዜ ድጋፍ ይደረግላቸዋል።

የኩዊንስላንድ መንግሥት የፈቀደላቸው የኪንዲ ፕሮግራሞች የሚቀርቡት ብቃት ባላቸው የህጻናት የቅድመ ልጅነት አስተማሪዎች ነው። የኪንዲ ፕሮግራሞች በቅድመ ልጅነት ትምህርት ማእከላት ውስጥ ሊሰጡ ይችላሉ፤ ወደ መዋለ ህጻናት ለመግባት እንቅፋት የነበሩባቸው የተመረጡ የገጠርና የሩቅ አከባባዎች እንዲሁም ሌሎች የተመረጡ የመንግስት ትምህርት ቤቶች፤ እንዲሁም ወደ አንድ ማዕከል መግባት ለማይችሉ አንዳንድ ልጆች በርቀት ትምህርት ወይም በኢ-ኪንዲ (e-kindy) ይሰጣሉ።

## በኪንዲ መማር

ኪንዲ ለህጻናት የሚከተሉትን ለማድረግ እድሎች ያቀርባል፡-

- ሀሳቦች፣ ስሜቶችን እና ፍላጎቶችን ለመግለጽ ቋንቋን መጠቀም
- ጓደኞች ማፍራት፣ ከሌሎች ጋር መግባባት እና መተባበር
- ችግሮችን መለየት እና ችግሮችን የመፍታት ችሎታ ማዳበር
- በብቃት ችሎታቸው በበለጠ እንዲተማመኑ እና በራሳቸው እንዲመሩ ማድረግ በችሎታቸው የበለጠ በራስ የሚተማመኑና በራስ የሚመሩ መሆን
- ከዓለማቸው ጋር ግኑኝነት መፍጠር፣ ማሰስና አስተዋጽኦ ማድረግ በዓለማቸው ላይ ካለው ጋር ለመገናኘት፤ ለመፈተሽና አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ
- እውቀታቸውን መገንባትና አዳዲስ ሀሳቦችን መፈተሽ፣ በራስ የመተማመን ለመገንባት ይረዳሉ እውቀታቸውንና አዲስ ሃሳቦችን ለመፈተሽ የሚረዳ ሙሉ እምነት ማዳበር

ስምተው ነበርን?

**Free KiNDY from 2024**

Free KiNDY

Queensland Government

# እንዴት መመዝገብ እንደሚቻል

በኩውንስላንድ ህጻናት የቅድመ ትምህርት ከመጀመራቸው ከአንድ ዓመት በፊት ወደ ኪንዲ መሄድ ይችላሉ።

እያንዳንዱ አገልግሎት የተለያየ ነውእና አንዳንዶቹ የመጠባበቂያ ዝርዝር ሊኖራቸው ይችላል። ስለዚህ ልጅዎን ለማስመዝገብ የትኛው ጥሩ ጊዜ እንደሆነ ከመረጡት አገልግሎት ጋር መነጋገሩ ጥሩ ነው።

ልጅዎ ኪንዲ ለመግባት በሚመዘገቡበት ዓመት ከ30 ሰኔ በፊት የ4 ዓመት ዕድሜ መሆን ኣለበት።

| የህጻን ምልክት | ህጻን ወደ ኪንዲ መሄድ የሚችለው |
|---|---|
| ከቀን 1 ሐምሌ 2019 እስከ 30 ሰኔ 2020 | 2024 |
| ከቀን 1 ሐምሌ 2020 እስከ 30 ሰኔ 2021 | 2025 |
| ከቀን 1 ሐምሌ 2021 እስከ 30 ሰኔ 2022 | 2026 |
| ከቀን 1 ሐምሌ 2022 እስከ 30 ሰኔ 2023 | 2027 |
| ከቀን 1 ሐምሌ 2023 እስከ 30 ሰኔ 2024 | 2028 |
| ከቀን 1 ሐምሌ 2024 እስከ 30 ሰኔ 2025 | 2029 |

ልጅዎን ለማስመዝገብ ምን እንደሚያስፈልግዎት፣

- የልጅዎን ስምና አድራሻ
- እንደ ወላጅ፤ ተንከባካቢ ወይም መጕዚት የርስዎን ዝርዝር መረጃ
- የሆነ የፍርድ ቤት ትእዛዝ ወይም የአሳዳጊነት ትእዛዝ ወይም እቅድ ካለ ዝርዝር መረጃ
- አስፈላጊ የሆነ ተጨማሪ ድጋፍ (ለምሳሌ፡ አካል ጉዳተኛ፤ የምግብ አለመስማማት ወይም ሌሎች ኣስፈላጊ ነገሮች) ካለ ዝርዝር መረጃ
- የትውልድ ቀን ማስረጃ (ለምሳሌ፡ የልደት ምስክር ወረቀት)
- የጤና እና የበሽታ መከላከያ ክትባት ሁኔታ
- ልጅዎን ከኪንዲ ማምጣት የሚፈቀድለት ሰው እና በድንገተኛ ጊዜ የምናሳውቀው ሰው ዝርዝር

የእርስዎ አገልግሎት ሰጪ ይሄንን መረጃ በሚስጢር ይጠብቃል፣ እርስዎ ደግሞ የልጅዎን መዝገብ ሙሉ በሙሉ ማግኘት ይችላሉ

# የኪንዲ ፕሮግራም ስለመምረጥ

በኩውንስላንድ ውስጥ ህጻናት በሙሉ የቅድመ ትምህርት ከመጀመራቸው አንድ ዓመት በፊት ተቀባይነት ባለው የመዋለ ህጻናት ፕሮግራም መሄድ ይፈቀድላቸዋል።

ተቀባይነት ያለው የመዋለ ህጻናት ፕሮግራም የመንግስት መመሪያዎችን ያሟላልእና በተጨማሪም:

- በመንግስት መመሪያ መሰረት በባለሙያ የቅድመ ልጅነት አስተማሪዎች የሚሰጥ የመማር መርሃግብር።
- አብዛኛውን ጊዜ በሳምንት ለ15 ሰዓታት፣ በዓመት ለ40 ሳምንታት፣ ከቅድመ ልጅነት በፊት ባለው ዓመት ለሚገኙ ልጆች ይሰጣል
- ከኩውንስላንድ መዋለ ህጻናት የትምህርት መመሪያ ወይም ከሌላ የኵውንስላንድ ስርዓተ ትምህርት እና ግምገማ ባለሥልጣን ተቀባይነት ካለው የመማር ማስተማር ፕሮግራም ጋር የተጣጣመ ነው

የኩዊንስላንድ መንግሥት ተቀባይነት ያለውን ፕሮግራም ለይቶ ለማወቅ እንዲያስችልዎት ከታች ያለውን የጸደቀ መሆኑን የሚያሳይ ምልክት ያለበት ‘kindy tick of approval’ የሚለውን ከስር ያለውን ምስል ፈልጉ።

FREE Kindergarten Approved Program

Queensland Government

# ከ2024 ዓ.ም ነጻ ኪንዲ

የኩዊንስላንድ መንግሥት ለሁሉም የኩዊንስላንድ ቤተሰቦች ኪንዲ ነፃ እያደረገው ነው።

ኪንዲ ከጥር 1 ቀን 2024 ጀምሮ ነጻ ኪንዲ በሚሰጡ በመንግሥት ተቀባይነት ያለው ፕሮግራም ላይ ለሚገኙ ዕድሚያቸው ተቀባይነት ያለው ልጆች ነፃ ይሆናል።

ይህ በሳምንት 15 ሰዓት፣ በዓመት 40 ሳምንት፣ በአንድ ብቃት ያለው የቅድመ ልጅነት አስተማሪ የሚሰጥ ነፃ ኪንዲ ነው።

ቤተሰቦች በአንድ በክፍለ ግዜ ኪንደርጋርደን የሚሰጥ ወይም በሙሉ ቀን መዋለ ህጻናት የሚያቀርብ ኪንደርጋርደን ኪንዲ መምረጥ ይችላሉ።

በአቅራቢያዎ ያሉትን የኪንዲ አቅራቢዎች ስለ ነጻ ኪንዲ ከ2024 ይጠይቋቸው።

Free KiNDY from 2024

በአቅራቢያዎ የሚገኝ ነጻ ኪንዲ ፈልገው ያግኙ፣ ይህን ድረገጽ: **www.qld.gov.au/FreeKindy** ይጎብኙ

230233